Washington State Department of Social & Health Services

Transforming lives

STATE OF WASHINGTON
DEPARTMENT OF SOCIAL AND HEALTH SERVICES
DIVISION OF CHILD SUPPORT (DCS)

የህጻን ድጋፍ ትዕዛዝ ግምገማ ጥያቄ
Child Support Order Review Request

ለ፡-

ጉዳዩ፥

የፋይል ቁጥር፡-

ቀን፥

የመርህግብር መረጃ

የልጅዎ ድጋፍ ትዕዛዝ እንዲሻሻል (እንዲቀየር) ወይም እንዲስተካከል የህጻናት ድጋፍ መምሪያውን (DCS) ጠይቀዋል። ትዕዛዝዎትን ለማሻሻል ወይም ለማስተካከል ሁለት አማራጮች አለዎት፡-

1. ትዕዛዝዎት እንዲሻሻል በመጠየቅ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ያስገቡ። በራዎ ወይም በጠበቃ አማካይነት ማድረግ ይችላሉ።
2. ትዕዛዝዎት እንዲገመገምልዎት DCSን ይጠይቁ።
   ሀ. ትዕዛዝዎትን በተመለከተ DCS እርስዎን ወይም ተቃራኒውን ወገን ሊወክል ወይም ጠበቃ ሊያቀርብ አይችልም።
   ለ. DCS መረጃዎትን ይገመግማል።
      (1) ትዕዛዝዎት ለግምገማ ለመቅረብ የሚያስችለውን ዝቅተኛ መስፈርት **ካላሟላ** DCS ምንም እርምጃ አይወስድም።
      (2) ትዕዛዝዎት ለግምገማ ለመቅረብ የሚያስችለውን ዝቅተኛ መስፈርት **ካሟላ** DCS ጉዳይዎትን (እንደአስፈላጊነቱ) ወደአቃቤ-ህግ ጽ/ቤት ወይም ሌላ የህጻን ድጋፍ ኤጀንሲ እንዲሻሻል ወይም እንዲስተካከል ይመራዋል። የሚከተሉት ዝቅተኛ መስፈርቶች ናቸው፡-
         (ሀ) ትዕዛዙ የሚመለከታቸው የሁለቱም ወገኖች ወቅታዊ አድራሻ ለ DCS መቅረብ አለበት።
         (ለ) ትዕዛዙ በሚመለከታቸው ሁለቱም ወገኖች ላይ የ Washington ግዛት ስልጣን ሊኖረው ይገባል።
         (ሐ) የድጋፍ መጠኑ ከተወሰነ ቢያንስ ሶስት አመታትን ማስቆጠር አለበት **ወይም** በሁኔታዎች ላይ መሰረታዊ ለውጥ እንደተፈጠረ ማሳየት አለብዎት። ግምገማው አሳዳጊ ያልሆነው ቤተሰብ ስለታሰረ የተጠየቀ ከሆነ ይህ መስፈርት ተግባራዊ አይሆንም።
         (መ) አሁን ባለው ትዕዛዝ ላይ ያለው አጠቃላይ የድጋፍ መጠን ወቅታዊ በሆነ በ ***Washington ግዛት የህጻናት ድጋፍ መርህግብር*** ላይ ከተገለጸው መጠን ቢያንስ 15 በመቶ በላይ ወይም በታች መሆን አለበት እንዲሁም። ግምገማው አሳዳጊ ያልሆነው ቤተሰብ ስለታሰረ የተጠየቀ ከሆነ ይህ መስፈርት ተግባራዊ አይሆንም።
         (ሠ) ለቀጣይ የትዕዛዙ ዘመን አጠቃላይ የድጋፉ መጠን ቢያንስ በ$2,400.00 መቀየር አለበት።

      ማሳሰቢያ፥ ከላይ የተገለጹት የመጨረሻዎቹ ሁለት መስፈርቶች ማግለያ ትዕዛዙ ለልጁ የጤና መድህን ሽፋን የመስጠት መስፈርት ከሌለው ነው።

በትዕዛዙ የተገለጸው ልጅ የመንግስት እገዛ ወይም የህክምና እገዛ የሚያገኝ ከሆነ ልዩ ደንቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

1. DCS ትዕዛዝዎትን በየ35 ወራቱ ለማሻሻል ወይም ለማስተካከል ወዲያው ይገመግማል። አሳዳጊ ያልሆነው ቤተሰብ የታሰረ ከሆነ DCS የድጋፍ ትህዛዝዎን ከ35 ወራት አስቀድሞ ሊገመግም ይችላል።
2. ትዕዛዝዎትን ያለ DCS እርዳታ ማሻሻል ወይም ማስተካከል ከፈለጉ ለ Washington ግዛት የተመደበውን የህጻን ድጋፍ በተመለከተ የተደነገገውን ደንብ የአቃቤ-ህግ ጽ/ቤት ወይም DCS ማጽደቅ አለበት።

DCS ትዕዛዝዎትን እንዲገመግምልዎት ከፈለጉ የዚህን ቅጽ ገጽ 2 እና 3 *መሙላት* እና *መመለስ* አለብዎት። ለተጨማሪ መስፈርቶች ገጽ 2 ላይ የሚገኙትን መመሪያዎች ይመልከቱ።

Washington State Department of Social & Health Services
Transforming lives

STATE OF WASHINGTON
DEPARTMENT OF SOCIAL AND HEALTH SERVICES
DIVISION OF CHILD SUPPORT (DCS)

የህጻን ድጋፍ ትዕዛዝ ግምገማ ጥያቄ
Child Support Order Review Request

የጠያቂ ስም፡- የጉዳይ ቁጥር፡-

መምሪያዎች

ማሻሻያ ወይም ማስተካከያ ለማድረግ ጉዳይዎት በ DCS እንዲገመገምልዎት ከፈለጉ ግምገማውን ለመጠየቅ ይህን ቅጽ ይጠቀሙ።

ከፊርማዎ በስተቀር ምላሽዎትን ይጻፉ። ጥቁር ወይም ሰማያዊ ቀለም ብቻ ይጠቀሙ።

ሁሉንም አስፈላጊ ቅጾች ፈርመው ለ DCS ይመልሱ። አድራሻው ገጽ 3 ላይ ተገልጿል። የህጻናት ድጋፍ ኤጀንሲ ከሆኑ ፈቃድ ያለው ተወካይ ቅጹ ላይ መፈረም አለበት።

የሚከተሉትን ቅጾች ሞልተው ይመልሱ፡-

1. የዚህ ቅጽ **ገጽ 2 እና 3**።
2. በ ***Washington ግዛት የህጻናት ድጋፍ መርህግብር ወርክሺት*** (ተያይዟል)። ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎት የተዘጋጀውን ክፍል ይሙሉ። የሌላኛውን ወገን የገንዘብ ሁኔታ መረጃ DCS ለማግኘት ይሞክራል።
3. ***የገንዘብ ሁኔታ ማሳወቂያ*** (ተያይዟል)። **የፍርድ ቤት ትዕዛዝ** ካለዎት ብቻ ይህን ቅጽ ይሙሉ።
4. ***የግላዊ መረጃ ቅጽ*** (ተያይዟል)። **የፍርድ ቤት ትዕዛዝ** ካለዎት ብቻ ይህን ቅጽ ይሙሉ።
5. ***ግላዊ መረጃ ጭማሪ ቅጽ*** (ተያይዟል)፣ ከሁለት በላይ ልጆች ካለዎት። **የፍርድ ቤት ትዕዛዝ** ካለዎት ብቻ ይህን ቅጽ ይሙሉ።

የሚከተሉትን ሰነዶች ያያይዙ። **ሰነዶቹ ከሌሉ ምክንያቱን የሚገልጽ ጽሁፍ ያያይዙ።**

1. የመጨረሻቹን ሁለት የፌደራል የገቢ ግብር ተመላሾች ቅጂ።
2. የመጨረሻቹን ሶስት የተበጣጠሱ ክፍያዎች ቅጂ።

ለ DCS የሚልኩትን ማንኛውም ሰነድ DCS ወይም አቃቤ-ህግ ለሌላኛው ወገን ሊያሳይ ይችላል እንዲሁም የፍርድ ቤት መዝገብ ውስጥ ሊያያዝ ይችላል።

1. ሌላኛው ወገን የእርስዎን የገንዘብ ሁኔታ የማየት መብት አለው።
2. ሰነዶቹን ለ DCS ከመላክዎት በፊት የግል የመታወቂያ መረጃዎችን (አድራሻ፣ የልደት ቀን፣ የማህበራዊ ደህንነት ቁጥር) ያስወግዱ።

የድጋፍ ትዕዛዜ እንዲሻሻ እና እንዲስተካከል DCS እንዲገመግመው የምፈልግበት ምክንያት (ለእርስዎ ጉዳይ የሚመለከተውን ከስር ካሉት ሳጥኖች ምልክት ያድርጉ)፡-

1. ☐ የገቢዬ መለወጥ።
2. ☐ የሌላኛው ወላጅ ገቢ መለወጥ።
3. ☐ በጉዳዩ ውስጥ ካሉት ልጆች ቢያንስ አንዱ፡-
   ሀ. ☐ ሌላ ቤት ውስጥ መኖር።
   ለ. ☐ ት/ቤት አለመሄድ ወይም ቤት መሆን።
4. ☐ የጤና መድህን መስፈርት ትዕዛዙ ላይ መጨመር አለበት።
5. ☐ አካል ጉዳተኛ ነኝ፣ ተቋም ውስጥ ነው የምኖረው ወይም እስረኛ ነኝ።
6. ☐ ሌላ (በዝርዝር ያቅርቡ)፡- _____

የሚከተለውን ተረድቼ ተስማምቼያለሁ፡-

1. የሚያስፈልገውን መረጃ በሙሉ ለ DCS ካልሰጠሁ DCS ትዕዛዙን አይገመግመውም።
2. ጉዳዬ እንዲሻሻል እና እንዲስተካከል DCS የሚገመግመው የልጆች የህጻናት ድጋፍ ወይም የጤና መድህንን በተመለከተ ነው። DCS ልጅ ማሳደግን፣ መጎብኘትን ወይም ሌላ ጉዳዮችን በተመለከተ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለመገምገም ስልጣን የለውም።
3. የህጻናት ድጋፍን ለማዘጋጀት፣ ለማሻሻል ወይም ለመተግበር DCS እኔ የሰጠሁትን መረጃ ይጠቀማል።
   ሀ. ለነዚህ አላማዎች ብቻ DCS ከሌሎች የመንግስት ኤጀንሲዎች ጋር መረጃ ይጋራል።
   ለ. DCS መረጃ የሚሰጠው የክልል እና የፌደራል ህጎች እና ደንቦች በሚፈቅዱት መሰረት ብቻ ነው።
   ሐ. የሌላውን ወላጅ የግል እና ሚስጥራዊ መረጃ ከ DCS መጠየቅ እችላለሁ።
4. DCS ጥያቄዬን ከገመገመ በኋላ ለአቃቤ-ህግ የሚያስተላልፈው፡-
   ሀ. በገጽ 3 ላይ የተጠየቀው መረጃ እና ቅጽ ሁሉ ለ DCS ከቀረበ።
   ለ. ጉዳዬ ለማሻሻያ እና ማስተካከያ ብቁ የሚያደርገውን መሰፈርት ካሟላ።

   ማሳሰቢያ፥ ለአቃቤ-ህግ የተላኩ ጥያቄዎችን ማቋረጥ አይችልም።
5. ትዕዛዜ የህግ ወይም የግምገማ መስፈርቶችን ካላሟላ DCS ወይም አቃቤ-ህግ የድጋፍ ትዕዛዜ እንዲሻሻል ወይም እንዲስተካከል ለፍርድ ቤት ከማቅረብ ሊቆጠቡ ይችላሉ።
6. የድጋፍ ትዕዛዜ እንዲሻሻል ወይም እንዲስተካከል አቃቤ-ህግ ከወሰነ የማንኛውም ለውጥ በስራ ላይ የሚውለው ማመልከቻው ለፍርድ ቤት ከገባበት ቀን ዳኛው ትዕዛዙን እስከፈረመበት ድረስ ባሉት ቀናት ነው። በስራ ላይ የሚውልበትን ቀን ዳኛው ይወስናል።
7. የተሻሻለው ወይም የተስተካከለው የድጋፍ ትዕዛዝ ከቀድሞው ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ የድጋፍ ክፍያ ሊሆን ይችላል።
8. የድጋፍ ትዕዛዜ እንዲሻሻል ወይም እንዲስተካከል ለፍርድ ቤት በራሴ ጥያቄ የማቅረብ መብት አለኝ።

_____ _____
ቀን የወላጅ ፊርማ

_____ _____
ቀን የወላጅ ተወካይ ፊርማ

_____
የወላጅ ተወካይ ስም ይጻፍ

DIVISION OF CHILD SUPPORT
PO BOX 11520
TACOMA WA 98411-5520

በ _____ ጥሪ ክልል ውስጥ _____
ከ _____ ጥሪ ክልል ውጭ _____
መናገር ወይመ መስማት ለተሳናቸው የTTY/TDD አገልግሎቶች አሉ::
ድረገፃችንን በሚከተለው አድራሻ ይጎብኙ: www.dshs.wa.gov/dcs

ማንም ሰው በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ ምንጭ ሃገሩ፣ ሃይማኖት፣ ጾታ፣ ዕድሜ ወይም የአካል ጉዳተኝነት የተነሳ የሥራ ቅጥር፣ አገልግሎቶችን በማግኘት፣ ወይም በማናቸውም የፕሮግራሙ እንቅስቃሴዎች መድልዎ ሊፈጸምበት አይችልም። ይህ ቅጽ በተለያዩ ቅርጸች ጥያቄው ሲቀርብ ማግኘት ይቻላል።

For Child Support Agency Use Only (ለህጻናት ድጋፍ ኤጀንሲ)			
AGENCY REPRESENTATIVE'S SIGNATURE		DATE	
AGENCY P.O. BOX OR STREET ADDRESS	CITY	STATE	ZIP CODE